ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ

ASSOCIATION FOR HUMAN RIGHTS IN ETHIOPIA

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን በድርጅታችንን ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ ላይ ጥሎ የነበረውን እገዳ ከ02/04/2017 ዓ.ም ጀምሮ ማንሳቱን አስመልክቶ የተሰጠ አጭር መግለጫ

ታሕሳስ 03 ቀን 2017 ዓ.ም

የተከበራችሁ የድርጅታችን አጋሮች እና ብዙኋን የድርጅታችን የሥራ እንቅስቃሴዎች ተከታታዮች በሙሉ፣ ሕዳር 03 ቀን 2013 ዓ.ም በሃገር በቀል ድርጅትነት በኢትዮጵያ ውስጥ ተመዝግቦ የህግ ሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅታችን ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ፤ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን በቀን 02/04/2017 ዓ.ም በጻፈው ደብዳቤ በድርጅታችን ላይ ጥሎ የነበረውን እገዳ ያነሳ መሆኑን የገለፀልን ሲሆን የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ እና የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት ከድርጅታችን ጋር በቅርበት በመነጋገርና በመወያየት የተፈጠረውን ችግር በአስተዳደራዊ መንገድ እንዲፈታ ላደረጉት ቀና ትብብር ምስጋና እናቀርባለን፡፡

ከእገዳው መነሳትም ጋር ተያይዞ ባለስልጣን መስሪያቤቱ ተፈጽመዋል ያላቸውን ግድፈቶች አስመልክቶ ማስጠንቀቂያ የሰጠን ሲሆን በዋነኝነት የቀረቡብን ገለልተኛ ያለመሆን እና ኃላፊነት በጎደለው መልኩ መንቀሳቀስ የሚሉት ክሶችን በተመለከተ ግን በማስረጃ ያልተረጋገጡ በመሆናቸው ማብራሪያ የምንጠይቀበት ይሆናል፡፡ አሁንም በድጋሚ ማረጋገጥ የምንፈልገው ድርጅታችን ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ ከተቋቋመበት ዓላማ ውጪ ከላይ በተገለጹት በማናቸውም ተግባራት ላይ ያልተሳተፈ እና በፖለቲካም ሆነ በሌሎች መሰል ጉዳዮች ላይ ፍጹም በሆነ ገለልተኝነት እንዲሁም የተመሰረተበትን ዓላማ መሰረት አድርጎ እና የአገሪቱን ህጎች አክብሮ ሲንሳቀስ የቆየ መሆኑን እየገለጽን በዚህ ረገድ በባለስልጣን መስሪያቤቱ በኩል ያሉ ብዥታዎችን ለማጥራት እና ግልፀኝነትን ለመፍጠር ጥረት የምናደርግ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለም፣ ድርጅታችን በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች በሚገባ እንዲከበሩ፤ የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ እና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን የተቋቋመበትን ዓላማ በቁርጠኝነት ለማሳካት እንደምንጥር በድጋሚ እያረጋገጥን ለዕግዱ መነሳት በምንሠራበት ወቅት ከጎናችን ሆናችሁ ቀና ትብብርና ያልተቋረጠ ድጋፍ ላደረጋችሁልን አገር በቀል እና አለም አቀፍ አጋሮቻችን እንዲሁም ብዙኋን የድርጅታችን የስራ እንቅስቃሴ ተከታታዮች ከፍ ያለ የከበረ ምስጋናችንን ለማቅረብ እንወዳለን፡፡

ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ